# ጎሞራው ሄደ አሉ ሳይሰናበተን

አሥራደው (ከፈረንሳይ)



በገንዘብ ሲኮራ - ሰው በወርቅ ሲያጌጥ፤
ጎሞራው በቅኔ - ነበር ይንቆጠቆጥ፤
ኩታው ነበር ቃላት - ካባው ነበር ስንኝ፤
ጎሞራው ሲቋጥር - ለወገኑ ሲቀኝ።
ሄደ አሉ ጎሞራው - ሁሉን ነገር ንቆ፤
ሊቀኝ ቅኔ ሊዘርፍ - ከዚች ዓለም ርቆ።

ሃቅ ነበር ጋሻው - ቃላት ነበር ጦሩ፤
በደል ኮሶው ሲሆን - ሰብዕና ነው ክብሩ፤
ጥበብን ኩታ አርጎ - ቃላት እንደ በትር፤
ነብስ እያስጨነቀ - ሥጋን የሚመትር፤
ከቆዳ ስር ዘልቆ - ልብ የሚቦረቡር፤
ጠጣሩ እንዲላላ - የላላ እሚወጥር፤
ያጥቢያ ፋኖ ወጊ - የብዕሩ ነብር፤
ጎሞራው፤ ጎሞራ፤ - **ጎሞራ!** ነበር።

እያንገጫገጨ - ምቾት የሚነሳ፤

ቃላት እየዘራ - ሃሳብ የሚያወሳ፤

ጠጣር ያ'ረግ አለት - የቋንቋ ወዝ ቅባት፤

ጉንጉን ያ'ሳብ ቅኝት - ሽርብርቦሽ ቃላት፤

በእሳት ተፈትኖ - ፈልቶ ሲወጣ ቃል፤

የነደደው ጨሶ ያረረው ይስቃል።

"ጎሞራው ሄደ አሉ ሳይሰናበተን፤

እንሸኘው ነበረ - ምንም ቢታክተን"።

ሃሳብ የሚያዋልድ - የሚያጭር ብልጭታ፤

ድንበር ሳይገድበው - በሄደበት ቦታ

አሳቢ ለወገን - ቋሚ ዋልታ ላገር፤

ጎሞራው ዝም አለ ዳግም ላይናገር።

" አገሬ ኢትዮጵያ ታጠቂ በገመድ፤

ጎሞራው ባዳ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ "።

ጎሞራው ባዳ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ "።

ለዕውቁ የስነ ጽሁፍ ሰው: ደራሲና ገጣሚ ኃይሉ ገብረዮሐንስ፤ **ጎሞራው** ማስታወሻ: የተቋጨች።

ሕዳር 6 ቀን 2007 ዓ.ም. (November 15/2014)